"ለጄኔራል አሳምነው አድርስልን?"

ዛሬ ወደ ወንዶች ጋራ ጎራ ብዬ ነበር።የጀግኖቼ አተጣጠቅ አሁንም በአይኔ ይዞራል። ለጀግኖቼ ድህንነት ሲባል ልዩ ቦታውን ትፍሸ አለልም።አዳሜ ፎቶ ከጠበቅሽም አለቅም። እንዲያውም የጀግኖቻችን ፎቶ ከአሁን በኋላ የለቀቀ የተወገዘ ይሁን እላለሁ።

እናም ጀግናውን የአማራ ገበሬ ጦር በአይኔ አየሁት።አንደበቴን ከፍቼ አናገርኩት።
ከፋኖ አርበኛው የአማራ (ጎንደር) ገበሬ ጦር መካከል፦ አንድ በእድሜ ጠና ያሉ አንድ እግር ክላሽኮፍ የታጠቁ አባት አየሁ።

ጤናይስጥል ብየ በወግ በማረጉ በትህትና ተዋወኳቸው።እነኝህን ቆፍጣና ነፍጠኛ አባት ቀስ እያልኩ አዋራኋቸው።ብዙ ዕርዕሶችን አንስተን ስናወራ ከቆዬን በኋላ ግን የመከላከያው ሚና ምንድነው? አለኳቸው።

"ልጄ" ብለው የተወሰነ ከቆዩ በኋላ፣በአመልካች ጣታቸው እየጠቆሙ "ያን ሸለቆ ታየው አለህ፣በሸጡ ውስጥ መከላከያ አለ።ይህ መከላከያ ቅማንቶቹ በሬ ሳይቀር አርደው ሲቀልቡት ይውላሉ" ነፍጠኛው ወጋቸውን ሳይጨርሱ...

ለምንድን ነው በሬ የሚያርዱላቸው? አልኩ።

"ልጄ ከዚህ ሸጥ ወደ 80 ሺ የቁም ከብት አለ።ይህ የቁም ከብት ደግሞ ከአማራ ህዝብ የተዘረፈ ነው።የአማራውን ከብት መከላከያው አብሮ አሳርዶ ጮማ ሲቆርጥ ይውላል።" የቆፍጣናውን ነፍጠኛ ጀሮዬን ቀስሬ እየተከታተልኳቸው ነው።ገለጻቸው ሌላ ነው።
ከአንደበታቸው የሚወጡት ቃላትና የአካል እንቅስቃሴያቸው ጥምረት ቀልቤን ስቦታል።

ጀሮዬን ብቻ ሳይሆን አፌንም ከፍቼ እያዳመጥኳቸው ነው።

ቆፍጣናው ነፍጠኛ ቀጠሉ "እየውልህ ልጄ መከላከያው የሚያግዘው ለተላለኪዎቹ ነው። የሚገርምህ መከላከያው እኛ ስንጠቃ ምንም አይልም።እንዲያው የደስደስ ነው መሰል ጥይት ፈጣሪን ናውረድ እያለ ወደ ሰማይ ሲተኩስ ይውላል።ነገርግ እኛ የህወሃት ጥቅመኞቹን ስናጠቃ መካከል ላይ ይገባል።እንዲያውም ልጄ ወደ እኛ ወግቶ ይተኩስብናል።ብዙ ወንድሞቻችን በመከላከያ ጥይት ቆስለዋል።ሙተዋል።"ሲሉኝ

ግን በሚታዩኝ መከላከያ ውስጥ የአማራ ተወላጆች የሉም?

"ልጄ አብዛኛዎቹ የትግራይና የቅማንት ተወላጆች ናቸው።አማራዎቹን እምብዛም ወደ ዚህ አይልኳቸውም።ሌላ ደግሞ የምነግርህ..." አሉ።

"መከላከያው ተኩሶ ብቻ አይደለም እየገደለን ያለው።ሌጀሩን ለቅማንቶች እያለበሰ፣እኛ መከላከያ ነው ስንል፣ቅማንት ሆኖ እየወጋን ነው።እየውልህ ልጄ እኛን የሚሰማን አጥተናል። ግን የሚሰማን የለም ብለን ዕርስታችን አናስከብርም አላልነም።እየውልህ ልጄ አሁን የምልህ ለጄኒራል አሳምነው አድርስልን? አይዋጉልን!! ግን ጥይት ያድርሱልን!!" አሉ ቆፍጣናው ነፍጠኛ ጅማታቸው እየተገታተረ!!

ይድረስ ብያለሁ!!

epnp.info

ኢሕብፓ
EPNP
የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

EPNP.INFO

